Global Storybooks


globalstorybooks.net

ማጎዝዌ

Lesley Koyi
Wiehan de Jager
Dawit Girma

This work is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License.
https://creativecommons.org/licenses/by/4.0

# ማጎዝዌ



Lesley Koyi
Wiehan de Jager
Dawit Girma

5

አማርኛ am



በተጨናነቀችው የናይሮቢ ከተማ በርካታ የጎዳና ተዳዳሪዎች ይኖራሉ። የስቃይ ኑሮ በየእለቱ ይገፋሉ፤ እያንዳንዱን ቀን እንዲሁ ይቀበሉታል። አንድ ቀን ጠዋት ልጆቹ ከመንገድ ዳር የተኙበትን ምንጣፍ ጠቀለሉ። ብርዱን ለመከላከል ቆሻሻ አንድደው እሳት ይሞቁ ነበር። ከልጆቹ ውስጥ ማጎዝዌ በእድሜ ትንሹ ነበር።



ወላጆቹ ሲሞቱ ማኅዝዌ ገና 5 ዓመቱ ነበር። ከአጎቱ ጋር ለመኖር ሄደ። አጎትዬው ግን ለልጁ አያስብለትም ነበር። ለማኅዝዌ በቂ ምግብ አይሰጠውም። ከባባድ ስራዎች ያሰራው ነበር።



ማኅዝዌ ካማረረ ወይ ጥያቄ ከጠየቀ አጎቱ ይገርፈዋል። ትምህርት ቤት ለመሄድ ሲጠይቅ አጎቱ ይመታውና እንዲህ ይላል፣ ‹‹አንተ በጣም ደደብ ነህ ምንም መማር አትችልም›› በእንዲህ አይነት ሁኔታ ሶስት ዓመታት ከቆዬ በኋላ አንድ ቀን ሮጦ ከአጎቱ አመለጠ። ጎዳና መኖርም ጀመረ።





ባለአረንጓዴ ጣራው ቤት ግቢ ውስጥ ቁጭ ብሎ ከትምህርት ቤት የወሰደውን የተረት መጽሐፍ ያነባል። ቶማስ መጣና አጠገቡ ተቀመጠ። ‹‹ተረቱ ስለምን ነው?›› ቶማስ ጠየቀ። ‹‹ታሪኩ አንድ መምህር ስለሆነ ልጅ ነው።›› ማኅዝዌ መለሰ። ‹‹የልጁ ስም ማነው?›› ጠየቀ ቶማስ። ‹‹ስሙ ማኅዝዌ ይባላል!›› አለ ማኅዝዌ በፈገግታ።




ማኅዘዌ ትምህርት ጀመረ፣ ግን ትምህርቱ ትንሽ አስቸጋሪ ሆኖበታል። አንዳንዴ ለማቋረጥ ሁሉ ይመኛል። ነገር ግን አየር አብራሪ እና ታዋቂ ኳስ ተጫዋች የሆኑትን በተረቱ ውስጥ ያሉትን ልጆች ያስባል። ልክ እንደነሱ ትምህርቱን ማቋረጥ የለበትም፣ እነሱ እንደሆኑት ሁሉ ያሰበበት መድረስ ይችላል።






የጎዳና ህይወት በጣም አስቸጋሪ ሲሆን ልጆች ምግብ ለማግኘት በየቀኑ ሲለፉ ይውላሉ። አንዳንዴ ይታሰራሉ፣ አንዳንዴ ደግሞ ይገረፋሉ። ሲታመሙ የሚያሳክማቸው ማንም የለም። ልጆቹ ኑሯቸውን የሚገፉት በልመና እና የወዳደቁ እንደላስቲክ አይነት ነገሮችን በመሸጥ በሚያገኙት ትንሽ ገንዘብ ነው። ከከተማው ሌላ ሰፈር ካሉ ሌሎች ጎዳና ተዳዳሪዎች ጋር የተሻለ ለማግኘት የሚያደርጉት ፉክክር ኑሯቸውን ይበልጥ ያመረዋል።



አንድ ቀን ማጎዝዌ የቆሻሻ ገንዳ ላይ እየፈለገ ሳለ አንድ የሆነ የተጎሳቀለና ያረጀ የተረት መጽሐፍ አገኘ። አጸዳዳውና በቦርሳው ከተተው። በየቀኑ መጽሐፉን ያወጣና ስእሎቹን ያያል። ማንበብ ግን አይችልም ነበር።






ከዚያም ማጎዝዌ ባለአረንጓዴ ጣራ ቤት ውስጥ ወዳለ አንድ ክፍል ሄደ። ክፍሉን ከሌሎች ሁለት ልጆች ጋር ነው የተጋራው። በቤቱ ባጠቃላይ አስር ልጆች ይኖራሉ። አብረውም ሲሲ እና ባሏ፣ ሶስት ውሻዎች፣ አንዲት ድመት እንዲሁም አንድ ያረጀ ፍየል ይኖራሉ።



ስጋቱን ለቶማስ አጋራው። ከጊዜ በኋላ ቦታው ትክክለኛና የተሻለ መሆኑን ቶማስ አረጋገጠለት።





ስእሎቹ ስለአንድ አውሮፕላን አብራሪ መሆንን እየተመኘ ስላደገ ልጅ ይተርካል። ማጎዝዌ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ነገር እንደቅዠት ያልም ጀመር። በተረቱ ውስጥ ያለው ልጅ ታሪክ የእሱ ይመስለዋል።



ቀዝቃዛ ነበር፤ ማኅዝዌም መንገድ ዳር ቆሞ ይለምናል። አንድ ሰው ወደእሱ እየተራመደ ሄደ። ‹‹ሰላም! ቶማስ እባላለሁ፣ እዚሁ አካባቢ ነው የምሰራው፣ አንተ ምግብ ማግኘት የምትችልበት ቦታ›› አለ ሰውየው። ቢጫ ቀለም ወደተቀባ ባለ ሰማያዊ ጣራ ቤት ጠቆመ። ‹‹ርግጠኛ ነኝ ወደዚያ ሄደህ ምግብ ትለምናለህ?›› ሰውየው ጠየቀ። ማኅዝዌ አንዴ ሰውየውን ቀጥሎ ደግሞ ቤቱን ተመለከተ። ‹‹ምናልባት›› አለ፤ ከዚያም ሄደ።





ማኅዝዌ ስለተጠቆመው አዲስ ቦታና ትምህርት ማግኘት ስለሚችልበት ሁኔታ ማሰላሰል ያዘ። አጎቱ ያለው ትክክል ቢሆንስ? ትምህርት መማር የማይችል በጣም ደደብ ቢሆንስ? እዚህ አዲስ ቦታ ከሄደ በኋላ ቢገርፉትስ? መፍራት ጀመረ። ‹‹ምናልባትም እዚሁ ጎዳና ላይ መሆን ሳይሻል አይቀርም›› ብሎ አሰበ።



የማኅዝዌ 10ኛ ዓመት ልደት ሲደርስ ቶማስ ለማኅዝዌ አዲስ የተረት መጽሐፍ ሰጠው። ዝነኛ እግር ኳስ ተጫዋች ስለሆነ በአንድ መንደር ይኖር ስለነበረ ልጅ ነበር ታሪኩ የሚያትተው። ቶማስ ይህን ታሪክ ለማኅዝዌ ብዙ ጊዜ አነበበለት፤ አንድ ቀን እንዲህ አለው፣ ‹‹እንደማስበው አሁን ትምህርት ቤት የምትገባበትና ማንበብ የምትማርበት ጊዜ ነው። ምን ታስባለህ?›› ቶማስ የልጆች ማቆያና ትምህርት ማግኘት የሚችሉበት ቦታ መኖሩን አብራራለት።





በቀጣዮቹ ወራት ጎዳና ተዳዳሪዎቹ ልጆች ቶማስን በአካባቢው መመልከት ለመዱ። ቶማስ ከሰዎች ጋር ማውራት ይወዳል በተለይ ከጎዳና ተዳዳሪዎች ጋር። ቶማስ የሰዎችን ታሪክና የህይወት ገጠመኝ ያዳምጣል። ቆፍጣናና ትእግስተኛ ነው፤ ትእቢተኛና ሰው የማያከብር አይደለም። አንዳንዶቹ ልጆች ወደ ቢጫና ሰማያዊው ቤት ምግብ ለማግኘት በእኩለ ቀን መሄድ ጀመሩ።



ማኅዝዌ መንገዱ ዳር እግረኛ መንገድ ጥግ ሆኖ ባለስእል የተረት መጽሐፉን እየተመለከተ ሳለ ቶማስ መጥቶ አጠገቡ ተቀመጠ ። ‹‹ተረቱ ስለምንድን ነው?›› ቶማስ ጠየቀ። ‹‹አንድ ፓይለት ስለሆነ ልጅ ታሪክ ነው›› መለሰ ማኅዝዌ። ‹‹የልጁ ስም ማነው?›› ጠየቀ ቶማስ። ‹‹አላውቅም፤ ማንበብ አልችልም እኮ›› አለ ማኅዝዌ ለስለስ ብሎ።





በተገናኙ ጊዜ ማኅዝዌ ታሪኩን ሁሉ ለቶማስ ያጫውተዋል። አጎቱ እንዴት እንዳደረገው እና እንዴት ማምለጥ እንደቻለ ይነግረዋል። ቶማስ ብዙ አያወራም፣ ማኅዝዌንም እንዲህ አድርግ እንዲያ አታድርግ አይልም፣ ዝም ብሎ በአትኩሮት ብዙ ያዳምጠዋል። አንዳንዴ ባለሰማያዊው ጣራ ትልቁ ቤት ምግብ ሲበሉም ያወራሉ።